አያሌው ቢታኔ በማናቸውም ፍርድ ቤቶች ጠበቃ እና የህግ አማካሪ

ቅፅ **1**

ባል ለሚስቱ የሚሰጣት ልዩ የውክልና ረቂቅ

ቀን ፡------------------------

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

አዲስ አበባ

<u>የዉክልና ስልጣን ማስረጃ</u>

ወካይ ፡- አቶ/ወ/ሮ፡-------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ ፡- --------------ከተማ------------ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ፡------------ የቤት ቁጥር፡-----------

ተወካይ፡- አቶ/ወ/ሮ፡--------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ ፡- --------------ከተማ------------ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ፡------------ የቤት ቁጥር፡-----------

እኔ ወካይ ተወካይ ባለቤቴ በመሆኗ የምሰጣት የዉክልና ስልጣን ተወካይ እንደ እኔ በመሆን በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘዉን ማንኛዉንም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረቴን በተመለከተ እንዲጠብቁ ፣ እንዲቆጣጠሩ ፣ እንዲያስተዳድሩ ፣ ዉል እንዲዋዋሉ ፣ገንዘብና ሰነድ ፈርመዉ እንዲቀበሉ ፣ እንዲያከራዩ፣ እንዲያኮናትሩ፣ የኪራይ ገንዘብ እንዲቀበሉ ፣የኪራይ ዉል እንዲዋዋሉ፣ ዉሉንም እንዲያፈርሱ፣ በስሜ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት አስይዘዉ ከማንኛዉም አበዳሪ ድርጅት ከባንኮች እንዲሁም ከግለሰብ በመያዣም ሆነ ያለመያዣ ገንዘብ ማበደርም ሆነ መበደር እንዲችሉ፣ የተበደሩቱንም ሆነ ያበደሩትን ገንዘብ ተሳስበዉ እንዲመልሱና እንዲቀበሉ፣ግብርም ሊዝም ሆነ ማንኛዉንም ለመንግስት የሚከፍሉ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ፣ በስሜ በማህበርም ሆነ በሊዝ ለመኖሪያ ቤትም ሆነ ለድርጅት መስሪያ የሚሆን ቦታ እንዲረከቡ፤ ካርታና ፕላን፣ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር እንዲያወጡ እንዲቀበሉ ፣ በስሜ የሊዝ ቦታ እንዲጫረቱ ለኢንቨስትመንት የሚሆን ቦታ እንዲረከቡ ፣ የግንባታ ፈቃድ እና የፕላን ማሻሻያ እንዲያወጡ፣ የግንባታ ስራዎችን ባለሙያ ቀጥረዉ ግንባታ እንዲያካሂዱ፣ ለግንባታዉ የሚያስፈልገዉን ማንኛዉንም ማቴርያል እንዲገዙ ፣ ስልክ፣ ዉሀ፣ መብራት እንዲያስገቡ ፣ ሊብሬ እንዲያወጡ ፣ ቦሎ ከላዉዲዮ እንዲያስደርጉ ፣አስፈላጊ ሲሆን የሰሌዳ ለዉጥ እንዲያደርጉ ፣ ሰሌዳ እንዲያስለጥፉ ፣ በስሜ የኢንቨስትመንት ፈቃድና ንግድ ፈቃድ ተመላሽ እንዲያደርጉ ማህተም እንዲያስቀርጹ ፣ ደረሰኝ እንዲያሳትሙ ፣ መንግስታዊ ክፍያዎች እንዲከፍሉ ማስረጃ እንዲሰጡ እንዲቀበሉ ፣ ዉል እንዲዋዋሉ እና ሰነድ እንዲፈርሙ ፣ ገንዘብ እንዲከፍሉ ፣ በስሜ በማንኛዉም ባንክ የተከፈተዉን የባንክ ሂሳብ እንዲያንቀሳቅሱ ፣ ገንዘብ ገቢና ወጭ ማድረግ እንዲችሉ ፣ ሂሳብን እንዲዘጉ በስሜ አዲስ የባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ ፣ ገንዘብ እንዲያስገቡ ፣ እንዲያወጡ ፣ ቼክ እንዲሰጡ እንዲቀበሉ ፣ ቼክ ላይ እንዲፈርሙ ፣ቼክ እንዲመነዝሩ ፣ ከማንኛዉም አካል የሚከፈለኝን ገንዘብ በቼክም ሆነ በጥሬ ገንዘብ እንዲቀበሉልኝ ፣ በስሜ በስምምነትና በሽርክና ዉል እንዲዋዋሉ ፣ አክስዮንም ሆነ ኩባንያ በስሜ እንዲያቋቁሙ በስሜ ዉል እንዲዋዋሉ እና ሰነድ እንዲፈርሙ ገንዘብ እንዲከፍሉና እንዲቀበሉ፣ የአክስዮንም ሆነ የኩባንያ ድርሻየን በጥሬ ገንዘብ ሆነ በቼክ እንዲቀበሉ በጥሬ ገንዘብ ሆነ በአይነት መዋጮ እንዲያስገቡ፣ ስብሰባ እንዲሰበሰቡ ፣ በቃለጉባኤ ፣በመተዳደሪያ ደንብ እና በመመስረቻ ጹሁፍ ላይ እንዲፈርሙ ፣ የአክሲዮን ድርሻየን እንዲሸጡ ፣ እንዲለዉጡ ፣ ድርጅቱን እንዲያፈርሱ ፣ ካፒታሉን እንዲያሳድጉ ፣ ኢንሹራስ እንዲገቡ ፣ ከኢንሹራስ የሚገኘዉን የካሳ ክፍያ እንዲቀበሉ ፣ ለኢንሹራስ የሚከፈሉ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ፣ ከኢንሹራስ ጋር ዉል እንዲዋዋሉ ፤ በስሜ የሚገኙ ማንኛዉም ሰነዶቸ የሚመለከተዉ የመንግስት መ/ቤት በመቅረብ ሰነዶችን እንዲያረጋግጡ ፣ በስሜ የልደት ሰርትፍኬትና የጋብቻ ሰርተፍኬት ፣ የቀበሌ መታወቂያ እንዲያወጡ ፣ እንዲያድሱ ፣ በዉርስ በፍርድም ሆነ በስጦታ የሚሰጠኝን የማይንቀሳቀስም ሆነ የሚንቀሳቀስ ድርሻ ንብረትም ሆነ ገንዘብ እንዲቀበሉ ፣ ስሙን ወደስሜ እንዲያዞሩ ፣ የድርሻ መልቀቅ ዉል እንዲዋዋሉ ፣ ድርሻየን እንዲረከቡ ፣ እንዲሸጡ ፣እንዲለዉጡ ፣ ስም እንዲያዛዉሩ ፣ዉል እንዲዋዋሉ ፣በስሜ ካሳ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ በአጠቃላይ በመንግስታዊ መ/ቤትም ሆነ ህዝባዊ ድርጅት፣ ግል መ/ቤት አስተዳደር መ/ቤት የኢትዮ ቴሌኮም ፣ሞባይል መምሪያ፤ በመብራት ኃይል ፣በዉሀና ፍሳሽ በመሬት አስተዳደር፣ በከተማ ልማት ፣ በፖስታ ቤት ፣ በቀበሌ፣ በሀገር ዉስጥ ገቢ፣ በዉጭ ጉዳይ መ/ቤት፣ በንግድና ኢንዱስትሪ፣ በኪራይ ቤቶች አስተዳደር፤ በባንኮች ፣በቤቶች ኤጀንሲ ፣በመንገድ ትራንስፖርት መ/ቤት ፣ክፍለ ከተማ ፤በወረዳ እንዲሁም በማናቸውም መንግስታዊ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ዘንድ እኔ ቀርቤ መፈጸም እና ማስፈጸም የሚገባኝን ጉዳዮች ተከታትለዉ እንዲፈጽሙ እና እንዲያስፈጽሙ በምከስበትም ሆነ በምከሰስበት አከራካሪ ጉዳይ ቢያጋጥም የህግ ጠበቃ ወክለዉ እንዲከራከሩ መልስ እንዲሰጡ ቃለማህላ እንዲያቀርቡ አፈጻጸም እንዲከታተሉ ማረጋገጫ እንዲፈርሙ ይግባኝ እንዲጠይቁ ዉሳኔ እንዲቀበሉ ፣ አስፈላጊ ሲሆን ለሌላ ሶስተኛ ወገን መወከልም ሆነ መሻር እንዲችሉ ፣ ይህንን ሙሉ የዉክልና ስልጣን በፍ/ብ/ህ/ቁ 2199/2205 መሠረት መስጠቴን በፊርማየ አረጋግጣለሁ ።

AYALEW BITANE ATTORNEY AND CONSULTANT AT LAW

አያሌው ቢታኔ በማናቸውም ፍርድ ቤቶች ጠበቃ እና የህግ አማካሪ

የወካይ ፊርማ

ቅፅ 2

የመኪና ሽያጭ እና አስተዳደርን የተመለከተ ልዩ የውክልና ረቂቅ

ቀን፡-----------------------------

በኢ.ፌዴሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

አዲስ አበባ

<u>የዉክልና ስልጣን ማስረጃ</u>

ወካይ ፡- አቶ/ወ/ሮ፡---------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ ፡- --------------ከተማ------------ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ፡------------ የቤት ቁጥር፡-----------

ተወካይ፡- አቶ/ወ/ሮ፡---------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ ፡- --------------ከተማ------------ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ፡------------ የቤት ቁጥር፡-----------

እኔ ወካይ ለተወካይ የምሰጣቸው ውክልና ተቀካይ በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን የሰሌዳ ቁጥር ኮድ ------------- የሻንሲ ቁጥር፡----------------- የሞተር ቁጥሩ---------------------- አይነቱ፡------------------ የሆነውን መኪናዬን ተወካይ እንደ እኔ በመሆን እንዲጠብቁ፣ እንዲቆጣጠሩ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ ሠሌዳ እንዲያስቀይሩ፣ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ ውል እንዲዋዋሉ ገንዘብ እንዲቀበሉ፣ ስም እንዲያዛውሩ፣የንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ፣ የንግድ ፈቃዱን እንዲያድሱ፣ ይህንን መኪና በተመለከተ የካሣ ክፍያ እና ኢንሹራንስ ሠነድ ላይ ፈርሞ ገንዘብ እንዲቀበልልኝ፣ ሊከፈሉ የሚገባቸውን መንግስታዊ ክፍያዎችና ግብር እንዲከፍሉ፣ ቦሎ ከላውዶ እንዲያደርጉ፣ ታርጋ እንዲያስለጥፉ፣ ሊብሬ እንዲቀበሉ፣ ለመኪናው ኢንሹራንስ እንዲገቡ፣ የኢንሹራንስ ክፍያ እንዲከፍሉ፣ የካሣ ክፍያዎችን እንዲቀበሉ፣ ክርክር ቢያጋጥማቸው የህግ ጠበቃ ወክለው እንዲከራከሩ፤ መልስና የመልስ መልስ እንዲሰጡ፤ ቃለ መኃላ እንዲያቀርቡ፤ ማረጋገጫ ላይ እንዲፈርሙ፤ ይግባኝ እንዲሉ፤ በአጠቃላይ በመንግስታዊ፣ በህዝባዊ፣ በአስተዳደር መ/ቤቶች፣ በመንገድ ትራንስፖርት መ/ቤት ፣ በግል ድርጅቶች በመቅረብ እኔ መፈጸምና ማከናወን የሚገባኝን ጉዳዮች ሁሉ ተከታትለው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፣ ሶስተኛ ወገን እንዲወክሉና እንዲሽሩ፣ይህንን የውክልና ስልጣን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 2199/2205 መሰረት መስጠቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ወካይ

AYALEW BITANE ATTORNEY AND CONSULTANT AT LAW

አያሌው ቢታኔ በማናቸውም ፍርድ ቤቶች ጠበቃ እና የህግ አማካሪ

ቅፅ **3**

የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ እና አስተዳደር የተመለከተ ልዩ ውክልና ረቂቅ

ቀን፡**-----------------------------**

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

አዲስ አበባ

<u>የዉክልና ስልጣን ማስረጃ</u>

ወካይ ፡- አቶ/ወ/ሮ፡---------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ ፡- ---------------ከተማ------------ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ፡------------ የቤት ቁጥር፡-----------

ተወካይ፡- አቶ/ወ/ሮ፡---------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

እኔ ወካይ ለተወካይ የምሰጣቸው የውክልና ሥልጣን ተወካይ እንደ እኔ በመሆን በስሜ ተመዝግቦ በ----------------- ከተማ በወረዳ -------- ቀበሌ ------------- ውስጥ የሚገኘውን የካርታ ቁጥሩ፡------------------------------------- የሆነውን የማይንቀሣቀስ ንብረቴን፣ እንዲጠብቁ፣ እንዲቆጣጠሩ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲሸጡ፣ እንዲለውጡ፣ እንዲያከራዩ፣ እንዲያኮናትሩ፣ ውል እንዲዋዋሉ፣ ገንዘብ በጥሬም ሆነ በቼክ ፈርመው እንዲቀበሉ፣ ቼክ እንዲመነዝሩ፣ በገዥ ስም እንዲያዛውሩ፣ ሊከፈሉ የሚገባቸውን መንግስታዊ ክፍያዎችና ግብር እንዲከፍሉ፣ በስሜ የግንባታ ፈቃድ እንዲያወጡ፣ የግንባታ ስራ ሙያተኛ ቀጥረው እንዲያሰሩ፣ ለግንባታ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችን እንዲገዙ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ስልክ እንዲያስገቡ፣ ክርክር ቢያጋጥማቸው የህግ ጠበቃ ወክለው እንዲከራከሩ፤ መልስና የመልስ መልስ እንዲሰጡ፤ ቃለ መኃላ እንዲያቀርቡ፤ ማረጋገጫ ላይ እንዲፈርሙ፤ ይግባኝ እንዲሉ፤ በአጠቃላይ በመንግስታዊ፣ በህዝባዊ፣ በአስተዳደር መ/ቤቶች፣ በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በክፍለ ከተማና በቀበሌ፣ በግል ድርጅቶች፤ በቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን፣ በውሃና ፍሳሽ፣ በመብራት ኃይል ባለሥልጣን መ/ቤቶች በመቅረብ እኔ መፈጸምና ማከናወን የሚገባኝን ጉዳዮች ሁሉ ተከታትለው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፣ ሶስተኛ ወገን እንዲወክሉና እንዲሽሩ፣ይህንን የውክልና ስልጣን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 2199/2205 መሰረት መስጠቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ወካይ

AYALEW BITANE ATTORNEY AND CONSULTANT AT LAW

ቅፅ 4

የጠበቃ ውክልና ረቂቅ

ቀን፡-----------------------------

በኢ.ፌዴሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

አዲስ አበባ

<u>የዉክልና ስልጣን ማስረጃ</u>

ወካይ ፡- አቶ/ወ/ሮ፡--------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ ፡- --------------ከተማ------------ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ፡------------ የቤት ቁጥር፡-----------

ተወካይ፡- አቶ/ወ/ሮ፡---------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ ፡- --------------ከተማ------------ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ፡------------ የቤት ቁጥር፡-----------

የጥብቅና ፈቃድ ቁጥር፡---------------

እኔ ወካይ ለተወካዩ የህግ ጠበቃ የምሰጣቸው የውክልና ሥልጣን በማንኛውም ፍርድ ቤት ቀርበው ክስ እንዲመሰርቱ፣እንዲከራከሩ፤መልስና የመልስ መልስ እንዲሰጡ፤ቃለ መኃላ እንዲያቀርቡ፤ማረጋገጫ ላይ እንዲፈርሙ፤ ይግባኝ እንዲሉ፤ አፈፃፀም እንዲጠይቁ፤ ውሣኔ እንዲያስፈጽሙ፣ ሰነድ ፈርመው መስጠትም ሆነ መቀበል እንዲችሉ፣ በአጠቃላይ በመንግስታዊ፣ በህዝባዊ፣ በአስተዳደር መ/ቤቶች፣ በግል ድርጅቶች፣ በመቅረብ እኔ ወካይ መፈጸምና ማከናወን የሚገባኝን ጉዳዮች ሁሉ ተከታትለው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 2199 መሰረት መወከሌን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ወካይ

____

AYALEW BITANE ATTORNEY AND CONSULTANT AT LAW

ቅፅ **5**

የውክልና መሻሪያ ረቂቅ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

አዲስ አበባ

<u>**የውክልና ስልጣን መሻሪያ**</u>

ሻሪ ፡- አቶ/ወ/ሮ፡---------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ ፡- --------------ከተማ------------ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ፡------------ የቤት ቁጥር፡-----------

ተሻሪ፡- አቶ/ወ/ሮ፡---------------------------------(ዜግነት ኢትዮጵያዊ

አድራሻ ፡- --------------ከተማ------------ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ፡------------ የቤት ቁጥር፡-----------

እኔ የውክልና ሥልጣን ሻሪው ለውክልና ሥልጣን ተሻሪው ከዚህ በፊት በዚሁ መ/ቤት ቀርቤ በውክልና ሥልጣን ቁጥር ፡--------------------------- በቀን፡--------------------ዓ.ም. የውክልና ሥልጣን ሰጥቻቸው የነበረ ሲሆን ይህንኑ የውክልና ሥልጣን ከዛሬ -------------------- ዓ.ም. ጀምሮ የሻርኩኝ እና ተሻሪውም መሻራቸውን እንዲያውቁ የመሻሪያውን ደብዳቤ በአድራሻቸው የማደርስ መሆኔን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2226 **መሠረት በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡**

የሻሪ ፊርማ

AYALEW BITANE ATTORNEY AND CONSULTANT AT LAW

AYALEW BITANE ATTORNEY AND CONSULTANT AT LAW